# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል
# 25 ኛ ሳምንት
# ኒቆዲሞስ

**ዓላማ**

- ስለኒቆዲሞስ እና ስለ ምሥጢረ ጥምቀት መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**

- *"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡"* ዮሐ.3÷5

**ምንባብ**

- ዮሐ 3÷5

**መግቢያ**

- እንደ ምድብ ሁለት ፤ ስለምሥጢረ ጥምቀትም እንማራለን፤

**ትምህርቱ**

- ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ለመማር በሌሊት የሚመጣ ኒቆዲሞስ የተባለ ምሁር ነበር፡፡
- የታወቀ ምሁር ሆኖ ሳል ስለጌታችን ለማወቅና ከእርሱም ለመማር አይሁድን ተሸሽጎና ፈርቶ ነበር ሌሊትም የሚመጣው፡፡
- አንድ ምሽትም ጌታችን ስለ ጥምቀት አስተማራቸው፡፡
- ታዲያ አንድ ቀን ኒቆዲሞስ በሌሊት መጥቶ *"መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዳመጣህ እናውቃለን፡፡"* አለው፡፡
- ጌታችንም *"እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም"* አለው፡፡
- ኒቆዲሞስም ተደንቆ *"ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?"* አለ፡፡
- ጌታችንም *"ዳግመኛ መወለድ"* ምን ማለት እንደሆነ አብራራለት፡፡ *"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፡፡ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው÷ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፡፡"* አለው፡፡

- በዚህ ትምህርት መሠረትም ቤተክርስቲያን ልጆችንና አዲስ አማንያንን ከውሃና ከመንፈስ ዳግመኛ ታጠምቃለች፡፡

- እናት ልጇን ታቅፋ ስትቀመጥ፤ካህናትና ዲያቆኑ ቆመው በማጥመቂያ ዙሪያ ይጸልያሉ፡፡የክርስትና አባትናእናትም ጸሎተ ሃይማኖት ደግመው ስለ እግዚአብሔር ሊያስተምሩ ቃል ይገባሉ፡፡ካህኑም የክርስትና ስም ይሠጣሉ፡፡ ***የክርስትና ስም ምንድነው?*** ተወያዩበት፡፡
- ተጠማቂው ሕጻን ከተጠመቀ/ች/በኋላ፤ሜሮን ይቀባሉ፤መንፈስ ቅዱስም ያድርባቸዋል፤ከውሃና ከመንፈስ መወለድ ማለትም ይህ ነው፡፡
- ጌታችንና መድኃኒኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኒቆዲሞስ እንዳስተማረውም ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም፡፡
- አዲስ ምሥጢር  እንደ ኒቆዲሞስ እንዲገልጥልንም፤ከእግዚአብሔር ለመማር ያለን ፍላጎት ሁሌም በጉጉት መሆን አለበት፡፡
- ኒቆዲሞስ ምሁር እንኳን ሆኖ ሳይኮራና ይበቃኛል ሳይል ይማር ነበር፡፡በዚህም ስለ ሰማያዊ ምሥጢር ተማረ፡፡

**ጥያቄዎች**

1.ኒቆዲሞስ ወደ ጌታችን ይሄድ የነበረው ለምንድነው?

2. መድኃኒታችንስ ስለ ምን አስተማረው?

3. ጥምቀት ምንድነው?

4. የተጠመቁ ሰዎች የሚወጣላቸው ስም ምን ይባላል?

**ተግባር**

- እንደ ኒቆዲሞስ የመማር ፍላጎት አላችሁ? ካልሆነ ለምን?

- ከመምህር እና ከቤተሰብ ጋር ተወያዩ፡፡ምክርም ተቀበሉ፡፡

**ይቆየን፡፡**